

# ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ለፋሲካ በዓል ወደኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ ነበሩ። ኢየሱስም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ወደአንድ መንደር ሄደው ገና ማንም ያልተቀመጠባትን አህያ ይዘው እንዲመጡ ላከቸው። ማንም ለምን ትወስዳላችሁ ብሎ ቢጠይቃቸው "ለጌታ ያስፈልገዋል፣ በቶሎ እንመልሳለን።"እንዲሉ አዘዛቸው።

ከብዙ አመታት በፊት አንድ ነቢይ "እነሆ ንጉስሽ እንደ የዋህ በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ ወደአንቺ ይመጣል።" ብሎ ተነበየ።

አህያይቱን ወደኢየሱስ አመጡለት ልብሳቸውንም ካለበሷት በኋላ ኢየሱስ ተቀመጠባት።
ኢየሱስ እየጋለባት ሲመጣም ሰዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ እያነጠፉ ይጠብቁት ነበር።
አንዳንዶች ደግሞ የዘንባባ ዝንጣፊ በመንገድ ላይ ያስቀምጡ ነበር። በዚህ መልክም ለሚመጣው ንጉስ መንገድን ያዘጋጁለት ነበር።

ብዙ ሰዎችም "ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ! በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው! ሆሳዕና በአርያም!" እያሉ ይጮኹ ነበር።

በተከታዩ ቀን ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ መቅደስ ገባ። በዚያም ሰዎች ከብቶችን በጎችና ፍየሎችን፣ እንዲሁም እርግቦችን ለመስዋዕት ይሸጡ ነበር። ኢየሱስም እጅግ ተቆጣ። በገመድም ጅራፍ አበጅቶ ከመቅደስ አባረራቸው። የገንዘብ ማስቀመጫ ጠረጴዛውንም ገለበጠው። በዚያ የነበሩትን እንስሳትም ከዚያ እንዲወጡ አደረጋቸው።

ኢየሱስም " ከዚህ ውጡ! እንዴት የአባቴን ቤት ወደ ገበያ ትለውጣላችሁ!" አለ።

ሕፃናቱም እንደገና “ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ ይሁን!” እያሉ ይጮኹ ነበር። የቤተ መቅደስ መሪዎችም ሕፃናቱ የሚጮኹትን ጩኸት ሰምቶ እንደሆነ ጠየቁት። እርሱም “ከሕፃናትና ከሚጠቡት ለራስህ ምስጋናን አዘጋጀህ ተብሎ ተፅፎአል።” ብሎ መለሰላቸው። ኢየሱስ የሕፃናትን ምስጋና መስማት ደስ ያሰኘዋል።

የኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዝ ታሪክ በማርቆስ ወንጌል በምዕራፍ 11፡ 1 – 19 ውስጥ ተፅፎአል።

http://gardenofpraise.com